**አርቲክል**

**በደፋሩ እምሬ**

## “ሰው ሆይ አንተ ትድን ዘንድ ምድርንም አድን”

“ኢትዮጵያ ሀገሬ ልምላሜሽ ማማሩ”
“ወንዞች ይፈሳሉ በየሸንተረሩ::”
“ኢትዮጵያ ለምለሚቷ”
“እኔስ ናፈቀኝ ያ ውበቷ::” ወዘተ. ወዘተ. እያሉ ብዙ ድምፃውያን ዘፍነዋል:: በዘፈን የሚታየውን ነገር ከመግለፅ፣ከማሞገስና ከመኮነን በስተቀር ልምላሜን፣ውበትን፣ወንዝን ማግኘት አይቻልም:: ድምፃዊያኑ እንዲህ ብለው የዘፈኑት በሁለት ነገሮች መነሻ ይመስለኛል::

የመጀመሪያው በክረምት ወቅት ዝናብ የሚያገኙ አዝርዕትና እፅዋት በሙሉ በቅለው፣አድገው፣ለምልመውና አብበው ሜዳውን፣እርሻውን፣ተራራውን፣ሸንተረሩን አረንጓዴ ስለሚያለብሱት ከዚያ ተነስተው ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ኢትዮጵያ ከ150 አመት በፊት 40 በመቶ የሚሆነው አካሏ በደን የተሸፈነ እንደነበር በታሪክ ከሰሙት ወይም በትምህርት ካገኙት ተነስተው ይሆናል:: በነገራችን ላይ በ1970ዎቹ ነው እነዚያ ድምፃውያን እንዲያ ብለው የዘፈኑት:: በዚያ ዘመን (ከ50 አመት በፊት ማለት ይቻላል) ኢትዮጵያ የተሻለ የደን ሽፋን ስለነበራት ልምላሜ፣ውበት፣በየሸንተረሩ የሚፈሱ ወንዞች እዚህ እዚያም ነበሯት:: ዛሬስ? መልሱን ለአንባቢያን ሰጠናል::

ዛሬ ዛሬ ክረምቱም ወቅቱን ጠብቆ እየገባ አይደለም:: የዝናብ እጥረት በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እየተከሰተ የሰብል ልማት ስራው እየተስንጎለ በቂ የምግብ እህል ማምረት ባለመቻሉ ሰዎች በተደጋጋሚ ለረሀብ ሲጋለጡ ማየት የተለመደ ሆኗል:: የአፈር ለምነቱም እንዲሁ ዛሬ ላይ እንደትናንቱ አይደለም:: ድርቅ ተበራክቷል:: በመጠጥ ውሃም ጉዳይ አለም እየተፈተነች ነው:: ይህ ሁሉ ምስቅልቅሎሽ ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ የህልውና አደጋ ደቅኗል:: ለዚህ በሰበብነት የሚጠቀሱ ተፈጥሯዊ ጉዳዮች ቢኖሩም የአንበሳውን ድርሻ የሰው ልጅ ራሱ ይወስዳል::

የሰው ልጅ ብዝኃ-ሕይወትን እያመናመነ፣ አካባቢውን እያዛባ፣ ምድርን እያጎሳቆለ... የዓለምን የምቹነት ዋስትና በራሱ እየተነጠቀ በመምጣቱ በመሬት ላይ ቆይታው ቀጣይነት ያለው ጤናማ

የሕይወት ዋስትና እንዳይኖረው በማድረግ በአንገቱ ላይ ሸምቀቆ አጥብቋል። ምድረ በዳ ወይም የተራቆተች መሬት ብዝሀ ህይወትን ማስተናገድ ስለማትችል የህልውና ዋስትና ከመሆን ይልቅ ምድራዊ ሲኦልነቷ ጎልቶ የሚያስተጋባ ይሆናል። ይህም እየመጣ እንደሆነ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰደው ከ120 አመታት በፊት ኢትዮጵያ ከአጠቃላይ ምድራዊ ስፋቷ 40 በመቶ በደን ኃብት የተሸፈነ እንደነበርና በሂደት ግን በብዝኃ-ሕይወት መመናመን ምክንያት ጥቅል የደን ሽፋኗ ወደ ሶስት በመቶ መውረዱ ታሪክ ያስረዳል። ይህ መጥፎ ገፅታ እንዲወገድና መሬት እጅግ ውብና ማራኪ የምድር ላይ "ገነት" ሲባል እንደሚደመጠው ከሞላ ጎደል እንድትሆን ማድረግ ከራሱ ከሰው ልጅ ይጠበቃል። "መድሀኒቴ ለህይወቴ…ለእኔ እንዳንች ፈዋሽ አልተገኘም ከቶ…" ሲል እንዳዜመው ድምፃዊ ለመሬት ፈዋሽ መድሀኒቷ ያለው በሰው ልጅ እጅ ነው ያሉ አርቆ አሳቢ ኢትዮጵያውያንና መሪዎቿ ዛሬ ላይ "አረንጓዴ አሻራ" የተባለውን ከሺህ አመታት በፊት ይተገብሩት እንደነበር ቀጥሎ የቀረበው ታሪክ ያስረዳል።

ከመካከለኛው ዘመን ታሪክ የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት መካከል አፄ ዳዊት ከ1375–1404 ዓ.ም በነበሩ የግዛት ዘመናቸው ደን ጭፍጨፋና የእንስሳትን አደን ለመከላከል በአገሪቱ ሰባት የአካባቢ ጥበቃ ጣቢያዎች አቋቁመው እንደነበር ዜና መዋዕላቸው ይናገራል። ልጃቸው አፄ ዘርዓ ያዕቆብም የአባታቸውን ፈለግ በመከተል በተለያዩ አካባቢዎች የደን ክምችት ጥበቃ አጠናክረዋል፤'የንጉሥ የደን ክልል' አሰኝተው ኢትዮጵያን የደን ካባ ለማልበስ ጥረዋል። ችግኞችን አፍልቶ የመትከል ሥራዎች ደግሞ በአፄ ልብነ-ድንግል ዘመነ-መንግሥት ስለመጀመራቸው ይወሳል።

ሌላው በደን ልማት ታሪካቸው የሚነሳው አፄ ምኒልክ ናቸው። የአፄ ዘርዓ ያዕቆብን 'የንጉሥ ደን ጥብቅ ሥፍራ' ጽንሰ-ሃሳብን አጠናክረዋል። በዘመናቸው ያጋጠማቸው የቤት መስሪያ እንጨትና ማገዶ እጥረት ለደን ልማት ተጨማሪ ኃይል ሆኖ የገፋፋቸው ይመስላል። አፄ ምኒልክ የደን የሕግ ማዕቀፍ አውጥተዋል፤ አማካሪም ቀጥረዋል። ደን ሁሉ የመንግሥት ንብረት እንዲሆንም ደንግገዋል። ባህር ዛፍን ከአውስትራሊያ አምጥተው በአዲስ አበባና አካባቢዋ በመትከል አዲስ ቸግኝ ወይም እፅዋትንም አስተዋውቀዋል። ባህር ዛፍ በፍጥነት ማደግ የሚችልና ራሱን በፍጥነት የሚተካ ተመራጭ ችግኝ መሆኑን አፄ ምኒሊክ ስለወደዱት ተክለውታል። /www.ena.et/web/amh/news/ላይ እንደተገለፀው አፄ ምኒልክ በመንግሥት ከሚለማው ደን በተጨማሪ ተራው ዜጋ በባለቤትነት በደን ድነና እንዲሳተፍም አዋጅ አውጥተው እንደነበር የመዕዋለ ዜና ዘጋቢያቸው ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ ወልደ አረጋይ

ጽፈዋል። አዋጁም ዛፍ የተከለ የመሬት ግብሩን ምሬዋለሁ የሚል ነበር። ለደን ጨፍጫፊዎችም ንብረታቸውን እንዲወረስና ብርቱ ቅጣት እንዲቀጡ ሕግ አርቅቀው እንደነበር ይወሳል። አፄ ምኒልክ ራሳቸው ከተከሏቸው ችግኞች መካከል በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን እና በደቡብ ወሎ ወረኢሉ ከተማ ይገኛሉ።

በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥትም ዛፍ መትከል ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ተግባር እንደነበር ይነገራል። በደርግ ዘመን የተከሰተው ድርቅና ረሀብ ደግሞ በኢትዮጵያ ለሌላ ተጨማሪ የችግኝ ተከላ ዘመቻ መንስዔ ሆኗል። በደርግ ሥርዓተ-መንግሥት ችግኝ ተከላ እንደ አፄ ምኒልክ ለችግኝ ተካዩ ማበረታቻ የሚያስጥ ተግባር ሆኖ እንደነበር ይነገራል። በአካባቢ ጥበቃ ጠንካራ የሕግ ማዕቀፎች ተቀርጸው ገቢራዊ ተደርገዋል። በወቅቱ የተደረገው የተራቆቱ አካባቢዎችን በተለይም ተራሮችን ዛፍ የመትከል ዘመቻ ፍሬ አፍርቷል። ዛሬ በበርካታ የአገሪቷ አካባቢዎች የደን ጸጉር የለበሱ ተራሮች ሕያው ምስክር ሆነዋል። የደርግ ዘመን አረንጓዴ አሻራዎች ዛሬ የተራሮች አረንጓዴ ዕንቁ ሆነዋል። በደርግ ዘመነ-መንግሥትም የአካባቢ ጥበቃን የተመለከቱ ፖሊሲዎች ተቀርፀዋል።

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከደን መመናመንና ከተፈጥሮ ኃብት መራቆት ጋር ተያይዞ አፍሪካና ኢትዮጵያ ያጋጠማቸውን ቀውሶችና ያለባቸውን ተግዳሮቶች ለምዕራቡ ዓለም አስረድተዋል፤ ተሟግተዋልም። አቶ መለስ "አረንጓዴ ኢኮኖሚ" እስከማለት ድረስ የዘለቁበትና ለምዕራቡ ዓለም ያስተዋወቁት ፓኬጅም የሚጠቀስ ነው። የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ቢኖሩም ዳሩ በዘመነ-ኢሕአዴግ በአገር ውስጥ ከፍተኛ የደን ውድመት የደረሰበት ወቅት እንደነበር ጥናቶች ይጠቁማሉ።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ መርሁ ያደረገውን "አረንጓዴ አሻራ "የኢትዮጵያ መንግስትም ይህን መርህ ከነስያሜው ወስዶ ለራሱ መተግበር ከጀመረችበት ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የወቅቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) አረንጓዴ ኢኮኖሚን፣ የአካባቢ ጥበቃንና የተፈጥሮ ኃብት መንከባከብን ትልቅ ትኩረት ሰጥተውታል። በሐምሌ 2011 ዓ.ም ያስጀመሩት የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በአራት አመት ውስጥ ከ20 ቢሊዮን በላይ ችግኝ መትከልን አላማ አድርጎ የተጀመረ ሲሆን አላማውም በስኬት ተፈፅሟል።

የሰው ልጅ ለመኖር አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት መሰረታዊ ፍላጎቶች ዋነኛ ምንጭም ናቸው፤እፅዋት ወይም ችግኞች። መሬትም ለሚኖርበት ሕዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የምግብ፣ውኃ እና መተዳደሪያ ምንጭ በመሆን ለሕይወታቸው፣ለደኅንነታቸው እና ለክብራቸው ወሳኝ ነው። ይህ እሙን የሚሆነው ደግሞ እፅዋትን ወይም ችግኞችን እየተከሉ ደኖችን መፍጠር እስከተቻለ ድረስ ብቻ ነው። ከዚህ አንፃር ለምድር ጤናማነት መመለስ አንዱና ዋናው ፍቱን መድሀኒት "የአረንጓዴ አሻራ"ፕሮጀክት እንደሆነ ቢሊዮኖች ይሁንታ ሰጥተውታል። አረንጓዴ አሻራ ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን ወይም የሚዋጅ ስያሜ ይሆናል ተብሎ ታምኖበት 193 ሉዓዋላዊ አገሮችን በአባልነት አቅፎ የያዘው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) በመርህነት ቀርጾ እያንቀሳቀሰው የሚገኝ ፕሮጀክት ነው።

ኢትዮጵያም በዚህ ስያሜው ዛሬ ላይ እየተገበረችው ቢሆንም "ችግኝ መትከል" ወይም "ደን ማልማት" በሚሉት ስያሜዎች ከ1000 አመታት በፊት ኢትዮጵያውያን ልማዳቸው አድርገው ይሰሩት እንደነበር እንደ ዶ/ር ተወልደ ብርሀን ያሉ የአካባቢ ጥበቃ ተመራማሪው ገልፀዋል። ችግኝ መትከል በዚህ ጊዜ ተጀመረ ለማለት ቢያስቸግርም በ14ኛው ክፍለ ዘመን በንጉስ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የኢትዮጵያ ህዝብ በራሳቸው ተነሳሽነት በዘመቻ ችግኝ ይተክሉ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል።

ከላይ እንደተገለፀው በአረንጓዴ አሻራው የተተከሉት ከ20 ቢሊዮን በላይ ችግኞች በሁሉም ክልሎች ተጠናክሮ በቀጠለው ፕሮግራም መሆኑን ልብ ይሏል። በአማራ ክልልም ባለፉት ሰባት የዚሁ ፕሮግራም አመታት (2017 ዓ.ም ጨምሮ) በተደረገው ርብርብ ከዘጠኝ ቢሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውን እና አረንጓዴ አሻራው ከመጀመሩ 2011 ዓ.ም በፊት 14 ነጥብ ሶስት በመቶ የነበረውን የክልሉን ደን ሽፋን ወደ 17 በመቶ እንደሚያሳድገው ከክልሉ ግብርና ቢሮ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

በአጠቃላይ "ችግኝ መትከል"፣ "ደን ልማት"፣ "አረንጓዴ ኢኮኖሚ" ፣ "አረንጓዴ አሻራ" የሚሉት ስያሜዎች "የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው" ነውና የአካባቢን ስነ ምህዳር በመጠበቅ ምርታማነትን ለማሳደግና ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን የተቃጠለ አየር መጠን በመቀነስ ንፁህ አየር ለመተንፈስ፣የከርሰ ምድር ውሃን በአስተማማኝ ደረጃ ለማግኘት ይረዳል።

በመጭው መስከረም 2018 ዓ.ም አጠቃላይ ግንባታው ተጠናቆ የሚመረቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በደለል እንዳይሞላ ደን ልማትም ተባለ አረንጓዴ አሻራም ከፖለቲካ ጨዋታና

ዘመቻ ወጥቶ ህዝቡ ቋሚ ባህሉ አድርጎ በየአመቱ እንዲተገብረው ማስረፅ ይገባል፡፡ እንዲህ ሲደረግ ነው፤ ኢትዮጵያ አረንጓዴ የምትለብሰው፤ አረንጓዴ አሻራም ዋጋና ተቀባይነት የሚኖረው፡፡

በመጨረሻም ይህን ያህል ሚሊዮን፣ቢሊዮን ተክልን ብሎ ለሚዲያ ፍጆታ አውሎ ማለፍ ሳይሆን መለስ ብሎ ያለፉትን ችግኞች መንከባከብ ይገባል፡፡ ለቀጣዮቹ የአሻራው ፕሮግራሞች ስኬትም የምግብ ዋስትናን በማገዝ የሚያረጋግጡ የፍራፍሬ አገር በቀል ዛፎችን በመትከል የሰው ልጅ ራሱንና መሬትን ማዳን ይኖርበታል፡፡ ዜጎች በዚህ ፕሮግራም በመሳተፍ አሻራቸውን ለአገራቸውና ለትውልድ ማስተላለፍ የሚችሉበት “ ሜዳውም ያው..” ነውና ተጠቀሙበት መልክታችን ነው፡፡